

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከሴፐቴምበር 1-10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምግማ

## እንዲሁም ከሴፐቴምበር 11-20 እና ከሴፐቴምበር 21-30/2025

## የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፐቴምበር


2025

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


## 1. እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት ለዝናብ መፈጠርና መስፋፋት አተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለይም በመጨረሻዎቹ ቀናቶች ላይ ተጠናክረው በመቀጠላቸው ዝናቡ በስርጭትም ሆነ በመጠን በብዙ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ክፍሎችን ያዳረሰ የዝናብ ሁኔታ ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 32፣ አዋሳ 33.4፣ በህር ዳር 33.7፣ 55.4፣ ደብረ ማርቆስ 49.4፣ ጎንደር 71፣ 38.6፣ መቀሌ 33፣ 36.5፣ አዲሰ አበባ ጥቁር አንበሳ 37.5፣ 59.8፣ አይራ 30.5፣ 47.3፣ አልጌ 43፣ አንገር ጉትን 64.6፣ 60፣ 34፣ አርጆ 46.4፣ 36.6፣ አርሲ ሮቤ 81.3፣ በደሌ 41.5፣ 43.4፣ ቡለን 30.4፣ 30.5፣ 46፣ ቻግኒ 50.4፣ ጨዋቃ 40፣ 30፣ ዳሊፋጊ 38፣ ደበረ ታቦር 37፣ ኢጃጂ 42.7፣ ፉኙንዶ 75፣ ጊዳ አያና 66.5፣ 32.6፣ ካቺሴ 38.9፣ ኮንሶ 33፣ ላሬ 51፣ ማንኩሽ 53.6፣ መተማ 34.6፣ ኘሁራ 42፣ ሽሬ 52.9፣ አቦ ሞሪንጋ 41፣ አታንጎ 34.5፣ 45.5፣ 31.2፣ ቢላምቢሎ 33.1፣ ቦርቃ 41.8፣ ቡልቂ 36.7፣ 30.2፣ መንደር ሰባት 146.4፣ ደበረ ሲና 43.9፣ 35.7፣ 34.3፣ ድልቢ 32.2፣ እርምጭ 35.7፣ ጋሸና 32.7፣ ጊናገር 43.9፣ ሃርቡ 30.2፣ 60.3፣ 30.2፣ ሆሮዶይ 46.4፣ ቅዳሜ ገበያ 48.6፣ 39.8፣ 56.4፣ 57.4፣ 48.7፣ 58.6፣ ኩሚ 33.8፣ ማርዬ 50.9፣ መቂ 63.2፣ ኦንጋ 37.5፣ 43.3፣ ሰቆጣ 35.6፣ ሸንዲ 34.5፣ 31.5፣ ተርኮዲ 103.2፣ ፅገሬዳ 33.7፣ ያንፉ 34.2፣ 41.3፣ 33.2፣ 45.3፣ ያዮ 31.8፣ መንድር 11 185፣ እንዲሁምየሪ 40፣ 30፣ ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ54 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 50.9 -185 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል መንደር 11፣ መንደር7፣ ተርኮዲ፣ አርሲ ሮቤ፣ ፉኙንዶ፣ ጎንደር፣ ጊዳ ኣያና፣ አንገር ጉትን፣ መቂ፣ ሃርቡ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከሴፕቴምበር 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የአዊ፣ የባህርዳር ዙሪያ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ61-370 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ፣ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሓረርጌ ዞኖች፤ የዋግ ህምራ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ የጋሞ፣ የወላይታ፣ ጌዲዮ እና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ ከ11-60 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ፣ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ሓረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎና የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ ጋሞ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ እና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ እና የሊበን ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

Ethiopian Meteorology Institute

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ በሆኑት የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ እና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተገኘው ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከመሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የክረምት ወቅታቸውን ጠብቀው ተዘርተው ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ባሉት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅና በደቡብ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታው የጎላ ነበር። በአንፃሩ በተከታታይ እርጥበት እያገኙ ባሉ አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከእርጥበት መብዛት ጋር በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት፣ የሰብል በሽታዎችና የአረም መስፋፋት የስከተለ ሲሆን አልፎ አልፎም በረዶ ቀላቀሎ ከጣለ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በሰብሎች ላይ መጠነኛ ጉዳትን አስከትሏል (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ሴፕቴምብር የመጀመርያ አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ መረብ ጋሽ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው አባይ እና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ ፣በላይኛው አዋሽ እና ባሮ አኮቦ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት አውንታዊ አስተዋፅዖ እንደ ነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወደ ግድቦች የሚገባውን ውሃ መጨመር ጥሩ ግብዓት ነበር፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው ኦጋዴን፣ አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ ገናሌ ዳዋ፣ መካከለኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሆነው ቆይተዋል (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ ሴፕቴምበር የክረምት የመጨረሻ ወር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየቀነሰ የሚሄድ ሲሆን፤ በአንጻሩ ለረጅም ጊዜ ደረቅ ሆነው የሰነበቱት የደቡብና የደቡብ ምሥራቅ አካባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን ማግኘት ይጀምራሉ። በዚህም መሠረት በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ100-300 ሚ.ሜ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚቀንስ በመሆኑ ከ12-23 ለሚደርሱት ቀናት ያህል ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት በሂደት እየቀነሰ የሚሄድ በመሆኑ ከ3-15 ቀናት ያህል ከ20-200 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል። የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ስፍራዎች ላይ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭት የሚጨምር በመሆኑ 30-100 ሚ.ሜ ከ3-12 ቀናት ይደርሳል፡፡


በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት የክረምት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚዳከሙ ሲሆንና፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ የወቅቱ ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በተመሳሳይ ሁኔታም የደቡብ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


Ethiopian Meteorology Institute

በመጪዎቹ የሴፕቴምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ(ካርታ 6)፡፡ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣

በመካከለኛዉ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እንደሚጨምር ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ካርታ 6 እና 7) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከሴፕቴምበር 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ቦረና ምስራቅ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| | የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ እና ባስኬቶ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በሴፕቴምበር ሶስተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከሰሜንና ከሰሜን ምሥራቅ ከሁለተኛው ሳምንት ጀምሮ እየተዳከሙ ስለሚመጡ ዝናቡ በመጠንም ሆነ በሥርጭትም ይቀንሳል፡፡ በሌላ በኩል የክረምት ዝናብ ድንበር (ITCZ) ወደ ምዕራባዊው አጋማሽና ወደ ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍሎች ስለሚያፈገፍግ ዝናቡ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በደቡብ እና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሁለተኛውን የዝናብ ወቅታቸውን ቀስ በቀስ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡

በሚቀጥሉት የሴፕቴምበር ሶስተኛዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እንዲሁም መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከቀን ወደ ቀን የደመና ሽፋን እየጨመረ እንደሚሄድ ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## 2.3 እ.አ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

Ethiopian Meteorology Institute

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በሰሜን ምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እንዲሁም በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ይህም የሚጠበቀው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፣ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

### ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• የአረም መስፋፋት<br>• የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት | • የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን በመጠቀም ትርፍ ውሀን ከማሳ ላይ ማሶገድ<br>• የአፈር መሸርሸር ስጋትን ለመቀነስ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር ምቹ ጊዜን ጠብቆ መተግበር |
| የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ዞኖች የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎችና ለቋሚ ተክሎችና እድገት | • የአረም መስፋፋት<br>• የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት | • አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር የአየር ሁኔታ ምቹነትን ባገናዘበ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት በቂ እርጥበት መኖር<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• የአረም መስፋፋት | • አረምን በወቅቱ ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |
| የአፋር ማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • የእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በመጠኑ መሻሻል | • በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን | • የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምስራቅ ባሌ፣ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ቦረና ምስራቅ ዞኖች የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ እና ባስኬቶ የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት | • ከፍተኛ ትነት መኖር | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |

## 2.4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

Ethiopian Meteorology Institute

በቀጣይ የሴፕቴምብር ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይጠበቃል። በመሆኑም በሚቀጥሉት ቀናት የሚኖረውን መልካም ዕድሎችን በላቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋልም ሆነ ተያያዥ አሉታዊ ተጽኖዎችን ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በየደረጃው መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የገጸ ምድር የውሃ ሽፋን | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው የተከዜ፣አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ መረብ ጋሽ፣ በላይኛው እና መካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት ላይኛው፣ ገናሌ ዳዋናና ዋቤ ሸበሌ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | • የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን መጨመር<br>• የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መጨመር<br>• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መጨመር<br>• የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል | • የወንዞች መሙላት<br>• የፍሳሽ መውረጃዎች በደለል እንዲሁም በጠጣር ቆሻሻ መዘጋት | ፍሳሽ ሊዘጉ የሚችሉ ቆሻሻዎች በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ<br>• የጎርፍ መውረጃዎች በዮችን ማፅዳት<br>• ወራጅ ውሀን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር |
| በአብዛኛው ኦጋዴን፣ ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ በታችኛው ኦሞ ጊቤና ስምጥ ሸለቆ | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ<br>• በከፍተኛ ሁኔታ የሙሉ ግድቦች ላይ የነበረው ጫና መቀነስ | • ዝቅተኛ የውሀ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት<br>• ከፍተኛ ትነት | • የሚገኘው መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>• የሚገኘውን መጠነኛ የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል |

Ethiopian Meteorology Institute